# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)
***Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)***

(ዴሞክራሲያዊ/Democratic)


ጳጉሜን 5 2001 ዓ.ም.

## እንኳን ለአዲሱ ዓመት ለ2001 ዓ.ም. አደረሰን!!!

**ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ፥ አዲሱ ዓመት ካምናው የተሻለ አዲስ ህይወት እንዲያመጣ "እንኳን ከዘመን ዘመን በሰላምና በጤና አሸጋገራችሁ" ማለቱ ለባህሉ ብቻ ሳይሆን ለአዲስ ተስፋና ለአዲስ ምኞት ጭምር መሆኑ እሙን ነው። ምንም እንኳን በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠረው ሕዝባችን ላለፉት አያሌ ዘመናት፥ እጅጉን ፈታኝ ወደ ሆኑ የኑሮ ሁኔታዎች እየተገፋ ቢሄድም፥ የዕለት ጉርሱን ልብሱንና መጠጊያውን ለማግኘት እጅጉን ቢቸገርም፥ አሮጌው ዓመት አልቆ አዲሱ ሲጀመር፥ ለወጉም ለባህሉም፥ እንዲሁም ለሁለንተናዊ አዲስ ጅማሮ እንኳን አደረሳችሁ መባባሉ የነበረና የቆየ ልማድ ነው። በዚህ አጋጣሚ ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያዊ) ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአዲስ ዓመት መልካም ምኞቱን በትህትና ይገልጣል።**

**እርግጥ ነው፤ አገራችን ኢትዮጵያ አላልፍላት ብሎ አስራ ሰባት ዓመት ያህል በመንግሥቱ ኃይለ ማርያም አምባገነን አገዛዝ ስር ከዳሸቀች በኋላ፥ ይኼው ሌላ አስራ ሰባት ዓመት ለሌላ አምባገነን ዘረኛና አሸባሪ አገዛዝ ተዳርጋለች። የአገራችንን ብሄራዊ ልዕልና ጥቅምና ድንበር እንደ አልባሌ ዕቃ ለሌላ አሳልፎ የሚሰጥ በታሪክ ተወዳዳሪ ያልተገኘለት ጉደኛ መንግሥት በአገራችን ላይ ከበቀለ እነሆ ለሁለት አሰርት ጥቂት ዓመታት ብቻ ቀርተውታል። ረጅሙ ሌሊት አልነጋ ብሎ፥ እንዲያውም ከአገዛዙ ብልሹነት ጋር ተፈጥሮም ተጨምሮና አድሞ፥ ዛሬ ወደ 14 ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝባችን በረሀብ አደጋ ምክንያት ሞትና ህይወት ዕጣ የሚጣጣሉበት እጅግ አሳዛኝ ሁኔታ ላይ ይገኛል።**

**ይሁን እንጂ በዚህ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ትንሽም ብትሆን ተስፋ የምትሰጠውን የብርሃን ጭላንጭል ለማየት ከቶውንም ሊሳነን አይገባም። በየትኛውም አገር ቢሆን ህዝቦች ከሚማቅቁባቸው የጭቆና ሁኔታዎች ውስጥ በአቸናፊነት ወደ ድል ሊጓዙ የቻሉበት ዋነኛ ምክንያት ተስፋን ምርኩዝ አድርገው፥ ዛሬም እንደ ትላንት አላፊ መሆኑን አምነው፥ የተሻለና አዲስ ህይወት፥ ለራሳቸውም ለልጅ ልጆቻቸውም ለማቆየት ባደረጉት ተጋድሎና ጥንካሬ ነው። የኛም ተስፋ እንዲሁ በማይጨበጥ እምነት ላይ የተመሰረተ አይደለም። በቅርቡ አትሌቶቻችን በ29ኛው የቤይጂንግ ኦሎምፒክ ላይ ካስገኙልን ድሎችና መላውን ህዝባችንን ካኮሩትና ካስደሰቱት ጉልህ ተግባራት በተጨማሪ ሁሌም ለኢትዮጵያ በጎ የሚመኙና ትንሳዔዋን ዳግም ለማብሰር ቀጣይ የትግል ችቦ ሊያቀጣጥሉ ዝግጁ የሆኑ የቁርጥ ቀን ልጆቿ መኖር ታላቅ የምስራች ነው።**


**850 Sligo Avenue Suite # 8 P.O.Box 8141 P.O.Box 88675**
**Siver Spring , MD 20910 Silver Spring, MD 20910 Los Angeles, CA 90009**
**Fax: 202-449-8363 Email Address: EPRP-Democratic@ eprp-ihapa.Com**

ያለፉትን የጨለማ ዓመታት መለስ ብለን በጥልቀት በምንመረምርበትና ለቀጣዩ ትግል በምንዘጋጅበት ባሁኑ ወቅት ተስፋ የሚሰጡ አንዳንድ አዳዲስ የፖለቲካ ክስተቶች ማየታችን ለኢትዮጵያም ለዜጎቿም ታላቅ ብስራት ነው፡፡ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ለአያሌ ዓመታት ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን ተሰልፈው ጨለማውን ለመግፈፍ ሲታገሉ የነበሩና ያሉ ልጆቿ የአገር ጥቅም ከፓርቲ ጥቅም በላይ መሆኑን ተገንዝበው፥ ካለፉት ስህተቶቻቸው ተምረው፥ እርስ በርስ እየተመካከሩ፥ እየተነጋገሩና እየተደማመጡ በመምጣት ላይ መሆናቸው የወቅቱ ተስፋ ሰጭ ሁኔታ ነው፡፡ ለሕዝብ እንታገላለን በሚሉ የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ኃይሎች መሀከል መከፋፈልና መለያየት የዘመኑ ወረርሽኝ ቢመስልም፥ ሊያስማሙና ሊያቀራርቡ በሚችሉ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ለየት ባለ መልኩ ለመደራጀትና በጋራ ለመቆም መፈለግ እየጎላ መምጣቱ ታላቅ የፖለቲካ ምስራች የሚያበስር ሁኔታ ብቻ ሳይሆን በእኩልነት ላይ የተመሰረተች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን በተግባር ለማየት ለሚሹ ሁሉ አበረታች ክስተት ነው፡፡ የኢትዮጵያም ህዝብ ድርጅቶቹን እየደገፈ እየተቸና እያበረታታ ሁሉም ዜጋ እጅ ለእጅ ተያይዞ የህወሓት/ኢሕአዴግን አገዛዝ ለአንዴና ለሁልጊዜ በማስወገድ “እንኳን ለአዲስ ዓመትና ለአዲስ ዴሞክራሲያዊ ጅማሮ አደረሰን” የምንባባልበትን ጊዜ በጋራ ለማምጣት መጣር የወቅቱ ብቸኛ አማራጭ ነው፡፡ በድጋሚ እንኳን ለአዲሱ ዓመት ለ2001 ዓ.ም. አደረሰን!

**የኢትዮጵያ ህዝብ ያቸንፋል!**
**የተባበረ ህዝብ አይበገርም!**
**መጪው ዓመት የኅብረት ትግልና የድል ዓመት እንዲሆን እንመኛለን!**

**850 Sligo Avenue Suite # 8** **P.O.Box 8141** **P.O.Box 88675**
**Siver Spring , MD 20910** **Silver Spring, MD 20910** **Los Angeles, CA 90009**

**Fax: 202-449-8363 Email Address: EPRP-Democratic@ eprp-ihapa.Com**